# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ጥር 24 ቀን 2003 ዓ.ም

## በጋራ ጥረት ዳግም የካቲት ዕውን ይሁን!

## ሕልውና ላላቸውና በእርግጥም ተቃዋሚ ለሆኑ ድርጅቶች ጥሪ፤

በአፍሪካ ሀገሮችና በመካካለኛ ምሥራቅም የጀመረው የለውጥና የሕዝባዊ አመፅ ነፋስ በኢትዮጵያም አረመኔውንና ዘረኛውን ሥርዓት ጠርጎና ሰባብሮ ያንኮታኩት ዘንድ በጋራ ሁሉም ህልውና ያላቸውና በእርግጥም ተቃዋሚ የሆኑ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች በተጨባጭና ተግባራዊ በሆነ መንገድ በኢትዮጵያ የጋራ እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዲተባበሩ ኢሕአፓ ይጠራል ።

ሕዝባችን ያለፈበትና ያለበት ሁኔታ በአሰቃቂነት ከተፈረጀና ከተገለፀ ዓመታት ያለፉ ሲሆን በአንፃራዊ ዕይታ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በተሻለ ደረጃ ያሉት ሕዝቦች ሲያምፁ ተመሳሳይና የባሰም ሕዝባዊ ቁጣ እስካሁን በሀገራችን ላለመከሰቱ አንዱ ዋና ምክንያት በአገዛዙ ላይ ቁርጥ ያለ አቅዋም ይዘው በፅናትና በድፍረት ለትግል የሚነሱ፤ ሕዝብን የሚያደራጁና ለትግል የሚጠሩ ድርጅቶች በቦታው ለመኖራቸው መሆኑን መካድ የሚቻል አይደለም። ይህን ድክመት ማስወገድ ከተቻለና የሕዝብ አመፅ በጋራ ከተሰናዳና ከተጠራ ውጤቱ የመለስ አገዛዝ ውደቅት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

ኢሕአፓ ሕዝብ በአመፅ እንዲነሳሳ በተደጋጋሚ እየጠራና ለዚህም ግብ በሁሉም መስክ እየተንቀሳቀሰ ነው። ተመሳሳይ ስምሪት ላይ ካሉ ድርጅቶች ተግባራዊ ቅንጅትን ማድረግ ጠቃሚ መሆኑንም ይገነዘባል። የየካቲት 66-ኡን የትግል መንፈስ ለማደስና የተባበረ ሰላማዊ ሰልፍ፣ የስራ ማቆምና ጠቅላላ አድማ፣ የሙት ከተማ አድማ፣ ...ወዘተ ለመጥራት ያመቻል።

ይህም ተግባር ወይም ትብብር በሀገር ቤት በትግሉ መስክ መሆን አለበትም ይላል። ይህ ሲረጋገጥ በባዕድ ሀገርም ያለው ፀረ የመለስ አገዛዝ ትግል እንዲሁ በተባባረ መልክ በስምምነት አቅጣጫ ሊጓዝ የሚችል ይሆናል። ኢሕአፓ ደግሞ ደጋግሞ እንደገለፀው የግንባር ሰነድ--በተለይም ህልውናና ይህ ነው የሚባል ሚዛን ከሌላቸው ቡድን ተብዬዎች ጋር--መፈራረም በአሁኑ ወቅት አስፈላጊም ጠቃሚም ነው ብሎ ባያምንም በተግባር ግን ሕዝባዊ አመፁን ለማቀጣጠል ፍላጎቱም ችሎታውም፤ በሀገር ቤትም ድርጅታዊ መዋቅር ካላቸው ጋር መደማመጥና ዳግም የካቲትን ዕውን ለማድረግ ሊተባበር ዝግጁ ነው። የተናጠሉ ጥረት በጋራውጥረት ቢተካ ውጤትን በጊዜ ማግኘት ይቻላል። መጪውንም የካቲት በሕዝባዊ ትግል በማክበርና የአገዛዙን ውድቀት በመሰዋዕትነት በማረጋገጥ የኢትዮጵያን ሕዝብንም በዓለም ሁሉ ማስከበር ይቻላል።


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France